


# ተልዕኮአችን

ግንቦት 2012 ቅጽ 1

ክርስቶስን ለመከተል መከራን ሁሉ
መቀበል ይገባል፤ እርሱ ያን ያህል
አስደናቂ ነውና!!

## የማይደክመው የአቅቤ- እምነት ሰው


## ዶ/ር ነቢል ቁረሺ

1983 – 2017 ዓ.ም

የጸሎት ጥሪ
አርጎባ ህዝብ ክፍል

ሚስዮናዊነት
እና የበሽታ ወረርሽኝ

የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ
እና የክርስቲያኖች ስደት



አንዳንዴ እግዜአብሔር እሩቅ
እንደሆነ የሚሰማን
ስሜት የመጣው እርሱን አርቀን
ስላስቀመጥን ነው፡፡ አርቀን
አስቀምጠነዋል እናም ልክ ጭንቅ
ውስጥ ስንገባ ናልኝ እያልን
እንጸልያለን
፤ የት ነው እያልንም ግራ እንጋባለን
አስተውሉ እርሱ እዛው እኛ
ያስቀመጥነው ቦታ ነው፡፡

# ዶ/ር ራቪ ዘካሪያስ

**1946 – 2020 ዓ.ም**

# መልዕክት

ተልዕኮአችን የተሰኘው ይህ ዲጂታል መጽሔት አማኞችን በወንጌል ዙሪያ ለማስተማር እና ለማገዝ የተጀመረ ነው ። ይህ ዲጂታል መጽሔት ወንጌል እና ተልዕኮ ዙሪያ ላይ ብቻ ጽሁፎችን፣ ትምህርቶችን እና መልዕክቶችን የሚያቀርብ እንደሆነ አቀድሜ ለማሳወቅ እወዳለሁ። በመጽሐይቱ ላይ በሚጻፉ ጹሁፎች እንደምትጠቀሙ እና ዕውቀትን እንደምትገበዩበት ዕምነቴ ነው። ይህ መጽሔይት በየ15 ቀኑ ዲጅታል በሆኑ መንገዶች በቴልግራም እና ሌሎች የማህበራዊ ትስስር ገጻች የሚለቀቅ ሲሆን የምታገኙባቸውን ቻናሎች እንደሚከተለው እገልጻለው።

Mission talk with Aman (https://t.me/NationsforGod)
Naoel's Perspective (https://t.me/NaolsP)
የቤሪያ ሰዎች በኢትዮጵያ (https://t.me/yeberiyasewoch)

በየ አስራ አምስት ቀኑ በእነዚህ የቴልግራም ቻናሎች እና በተለያዩ የማህበራዊ ትስስር ገጻች ይለቀቃል። መልካም ንባብ እንዲሆንላቹ እመኛለው ።

በተጨማሪም ጥያቄ እና አስተያየት ካልዎት
በስልክ ቁጥር :- +251920293652/ +251940094767 ይደውሉ
ኢ-ሜይል :- trsionamanuel9@gmail.com
ያግኙን

አማኑኤል ገዛኸኝ
አስተባባሪ

# ማውጫ


ገጽ

የማይደክመው የአቅቤ- እምነት ሰው 1

የጸሎት ጥሪ አርጎባ ህዝብ ክፍል 9

ሚስዮናዊነት እና የበሽታ ወረርሽኝ 7

የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ እና የክርስቲያኖች ስደት 11





*1983 – 2017 ዓ.ም*

# ዶ/ር ነቢል ቁረሺ

## የማይደክመው የአቅቤ- እምነት ሰው

ታሪክ የማይረሳቸው ታሪከኞችን ስናስታውስ ነቢሊ ቁረሺን የመሰለ የወንጌል ጀግኖናን መርሳት ከባድ ነው፡፡ ሴፕቴምበር 16- 2017 አምለክ ልጁን የጠራበት ቀን ነበረች የህመሙን ዜና ከሰማሁባት ቀን ጀምሮ በብዙ አዝኜ ነበር ፡፡ በሞቱ ወዳምላኩ እንዲሄድ ባውቅም በህይወቴ ላገኛቸው ከምመኛቸው ሰዎች ውስጥ ስለነበር ነው፡፡ የህይወት ምስክርነታቸውን ደጋግሜ ብሰማም ሁሌም ከምደነቅባቸው ሰዎች ውስጥ ነቢል ቁረሽ አንዱና ዋናው ነው፡፡ ዛሬ "ሲኪንግ አላህ ፋይንዲንግ ጂሰስ" ወይም "አላህን ስፈልግ እየሱስን አገኘውት" የሚለውን መጸሐፉን ሳነብ ይበልጥ የዚህ የወንጌል ጀግና ማለፍ ተሰማኝ፤ አንድንም ነገር አሰብኩ ማን ነው ተረኛው ነቢል ቁረሺ? እውነትን ፈልጎ ያገኘ፣ ይህን እውነት ደግሞ ለጨለማው ዓለም ለማድረስ የሚተጋ ማን ይሁን ተረኛው ነቢል ቁረሺ? ይህን ጥያቄዬን ደግሞ ነቢል ቁረሺ ያገለግልበት የነበረውን መንፈሳዊ አገልግሎት የመሰረቱት ዶ/ር ራቪ ዘካርያ ወደ ሚወዱት እና ወዳገለገሉት ጌታ እንደሄዱ ስሰማ ይበልጥ እንድጠይቅ አደረገኝ ? ማነው ተረኛው ራቪ ዘካርያስን ጨመርኩበት በእነዚህ የወንጌል አርበኞች አገልግሎት ብዙ ሺዎች በተለይ በእስልምና አለም ውስጥ ያሉ ሰዎች እውነት በርቶላቸውል፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለሰው ልጆች የሆነውን ድህነት ተቀብለዋል፡፡ በቀጣይ በዶ/ር ራቪ ዘካርያስን ታሪክ እና የአገልግሎት ጉዞ ለማቅረብ አስባለሁ በዚህ ጽሁፍ ግን የዶ/ር ነቢል ቁረሽን ታሪክ እና አገልግሎት ጉዞ በአጭር ላጋራችሁ ወደድኩ፡፡
መልካም ንባብ!

ነቢል ቁረሺ ካሊፎርኒያ ግዛት ሳንዲያጎ ከተማ በ1983ዓ.ም ከፓኪስታን ወደ አሜሪካ በገቡ ከስደተኛ ቤተሰቦቹ ተወለደ፡፡ ከአባቱ የባህር ሃይል ሰራተኛነት የተነሳ ቨርጂኒያ ግዛት እስካረፉበት ግዜ ድረስ በልጅነቱ ብዙ ቦታዎችን እየተዟዟሩ ኖረዋል፡፡ ጥብቅ በሆነ የእስልምና ዕምነት ተከታይ ቤተሰብ ውስጥ ተወልጆ እንዳደገ ይናገራል ለዚህ ደግሞ አያቱ እና ቅድመ አያቱ ምዕራብ አፍሪካ እና ኤንዶኔዢያ የኢስላም ሚሲዬናውያን ሆነው እስልምናን ካስፋፉ አንቱ ከተባሉ ሰዎች አንዱ መሆናቸው እንደ ምክኒያት ይነሳል፡፡ ቤተሰቡም አሜሪካ ለረጅም አመታት ይኑሩ እንጂ የምዕራባውያንን ባህል ላለመጋራት ጥብቅ በሆነ ኢስላማዊ ስርዓት እና ትምህርት ኖረዋል፡፡ ነቢልም በአስተዳደጉ እነዚህን ስርዓቶችን እና አስተምሮዎችን መጠበቅ ከሁሉ በላይ እንደሆነ እየተነገረው እና እየተገበረው ኖሯል በአንድ ፕሮግራም ላይ ነቢል ስለአስተዳደጉ ሲያወራ እንዲህ ይላል እናቴ ሁሌም እንዲህ ትለኛለች ነቢል በምትሄድበት ቦታዎች ሁሉ ትምህርት ቤት፣ መንገድ ላይ ሰዎች ገና ፊትህን እንደዳዩ እንዲም ይላሉ እርሱ ሙስሊም ነው ስለሆነም አንተ የእስልምና አምባሳደር ነህ ስለዚህም እስልምናን በሚገባ ልትወክል እና ልታሳይ ይገባሃል፣ በትምህርት ቤትህ በጣም ሰው አክባሪ መሆንህን እርግጠኛ ሁን አስተማሪዎች ከክፍላችሁ ካሉ ተማሪዎች በላይ አክባሪ እና ስነስርዓት ያለህ ተማሪ መሆንህን ማየት አለባቸው ምክኒያቱም አንተን በሚያዩበ መንገድ ነው እስልምና ማለት ይህ ነው ብለው የሚተረጉሙት፣ የማትዋሽ እና በስብዕናህ የላቅ ልጅ መሆንህ አሳይ ትለኛች ፡፡

ከዚህ ባለፈ ቤተሰቦቼ በጣም ጥሩ እና መልካም የሆነ ሙስሊም እንድሆን አስተማሩኝ ይህም ማለት ደግሞ የእስልምናን አስተምሮዎች መከተል ነው፡፡ ይህ እንዴት መሰላችሁ ለማሳሌ ስምንተኛ ክፍለ ሆኜ ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ እግሬ ከአልጋው ወርዶ መሬት ሳይነካ እናቴ ያስለመደችኝ ጸሎት አለ ፣ ከዛም ወርጄ ወደ መጸዳጃ ቤት ከመግባቴ በፊት ግራ እግሬ ቀድሞ መግባቱን አረጋግጣለሁ ይህ ምን ያህል ቤተሰቤ የእስልምናን ስርዓቶች አጥባቂ እንደነበር ያሳይል፡፡ በታሪክ ነቢዩ መሀመድ ወደ መጸዳጃ ቤት ሲገባ ግራ እግሩን አስቀድሞ እንደነበር ይነገራል መሀመድ ይህን ካደረገ እርሱ የፈጣሪ መልዕክተኛ ነውና እኛም እናደርገዋለን ነው ይህ የመሰጠታችን ልክ ነበር፣ መጸዳጃ ቤት ከገባሁም በኃላ "ዉዱ" የተሰኘውን የመታጠብ ስርአት ፈጽማለሁ በዚህም በቀን ውስጥ ካሉ አምስጥ ጸሎቶች ለአንደኛው እራሳችሁን ታዘጋጃላችሁ፣ ለመጸለይም ምንጣፌን እያዘጋጀው ከጸሎቱ በፊት የምፀልያቸው ጸሎቶች አሉ እነርሱንም ስጨርስ ነው የቀኑን የመጀመሪያ ጸሎት ምጸልየው ይህ ሁሉ ደግሞ በአረብኛ ነው፤ ጸሎቶቹም ሁሉ እኔ ከልቤ ምጸልያቸው ሳይሆኑ የሸመደድኳቸው ናቸው፣ ከዛም ለቁርስ እቀርባለው ከመብላቴ በፊት እጸልያለው ከዛም እናቴ ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ስወጣ ትከተለኝና ሙሴ ለፈንኦን ከመናገሩ በፊት እግዚአብሔር ድፍረት እና ጥበብ እንዲሰጠው የጸለየውን ጸሎት መጸለይ አትርሳ ትለኛለች ይህንንም ወደ ትምህርት ቤት እየሄድኩ ዘውትር እጸልያለው፡፡ ይህ የእያንዳንዱ ቀን ተግባሬ ነበር ይህ ብቻ ሳይሆን የቁርአኑን የመጨረሻ ሰባት ምዕራፎች በአምስት አመቴ በቃሌ መናገር እችል ነበር ምክኒያቱ ደግሞ በቀን ውስጥ ባሉ አምስት ጸሎች የምንጸልያቸው ስለነበሩ ነው፣ በ15 ዓመቴ ደግሞ የቁርአኑን የመጨረሻ 15 ምእራፎችን በቃሌ ይዤ ነበር ፣ ሙሉ ቁርዓንን ደግሞ በአረብኛ በአምስት አመቴ አንብቤአለሁ ይህ ምን ያህል ጠንካ ሙስሊም ቤተሰብ እና የኃላ ታሪክ እንዳለኝ እንድታዩ ነው ፡፡

ይህ ግን ሌላ ተቃራኒ ጎን ነበረው እናቴ ሁሌም አንተ የኢስላም አንባሳደር ነህ ስትለኝ ወደ ትምህርት ቤት ሄጄ ሌሎችን ስለእስልምና እንዳስተምር፣ እንድሞግት እና ወደ እምነቱ እንድጋብዝ ነበር፡፡ ስለዚህም ወንጌል አማኞች ስለ ክርስቶስ ወንጌል ሊነግሩኝ በሚሞክሩ ግዜ እኔ የተጋጁ ጥቅሶች እና መልሶች ነበሩኝ ፡፡ አስታውሳለሁ አስራ አንደኛ
ክፍል ሁኜ አንዲት ቤትሲ የተባለች የክፍል አጋሬ ስለ ክርስቶስ ልትነግረኝ ሞከረች እንዲህም ጠየቀችኝ እየሱስን ታውቀዋለህ ብላ እኔ ግን ተዘጋጅቼ ነበርና አዎ አውቀዋለው አልኳት በቁርዓናችን መሰረት ኢየሱስ ከድንግል እንደተወለደ፣ ብዙ ድንቅ ተዓምራትን እዳደረገ፣ እንደፈወሰ፣ ሙታን እንዳስነሳ፣ መሲሁ እንደሆነ በዘመን ፍጻሜም ደግሞ ተመልሶ እንደሚማጣ አምናለው አልኳት በድንጋጤ ትመለከተኝ ጀመር ሙስሊሞች ይህን እንደምናም እውቀቱም አልነበራትምና እኔም ይህን ተጠቅሜ እየሱስ ግን አምላክ አይደለም አልኳት ይህ ለሙስሊሞች ትልቅ ሃጢያት እና ክህደት ነውና፤ እርሷም አይደለም ነቢል ብላ ልታስረዳኝ ሞከረች እኔም እስኪ ኢየሱስ የቱ ጋር ነው አምላክ ነኝ ያለው ብዬ ጠየኳት ልታስረዳኝ ሞከረች ግን መልሷን አጣጣልኩት እርሷም ዝምታ ወረሳት እኔም ቀጥዬ ቤትሲ ስለክርስቶስ ማወቅ ከፈለግሽ ስለ እስልምና ጠይቂኝና አስተምርሻለው አልኳት ለዚህች ልጅ ያለኝ አክብሮት ግን እጅክ ከፍ አለ ፤ ለረጅም አመት ክርስቲያን ጓደኞቼ ስለክርስቶስ ነግረውኝ አያውቁም ጥያቄም ይፈጥርብኝ ነበር ቆይ ስለዕምነታቸው ግድ አይላቸውም እንዴ ሚል ጥያቄ ይፈጠርብኝ ነበር፡፡

ታዲያ በእንደዚህ ጥብቅ የእስልምና አስተምሮ እና ልምምድ ያደግገው ነቢል ቁረሽ እንዴት ለኢየሱስ እጁን ሊሰጥ ቻለ፡፡ ለዘመናት እውነት ብሎ የተከተለው እና ለብዙዎች ያጋራውን እስልምና ትቶ ሌላ የሚበልጥ መልዕክት የተሻለ እውነት መዳኛ መንገድ አለ ብሎ ሊያስተምር ሆነ ፡፡ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሆኖ ከዘብዙ ክርስቲያኖች ስለ መዳኛ መንገድ ያወራ ነበር ከብዙ የተለያዩ እምነት ተከታዬች ጋር ግዜ ያሳለፍ ነበር ካገኛቸው ሰዎች ሁሉ ውስጥ ግን ከአንድ ልጅ ጋር ጥሩ ቀረቤታ መሰረተ ዴቪድ ይባላል ይህም የሆነው ዴቪድም እንደርሱው ለእምነቱ ትልቅ ቦታ ይሰጥ ስለነበር ነው፡፡ ነገሮችን ሁሉ የቀየረች አጋሚም ልዩ ነበረች ፡፡

ከዴቪድ ጋር በክርክር ቡድን ውስጥ አንድላይ ነበሩ በዚያች አጋጣሚም አንድ ምሽት አንድ ክፍል ውስጥ አብረው ለማደር ገቡ ነቢል ሲናገር እኔ እናቴን ስልክ አወራው ዴቪድ ደግሞ መጸሐፍ ቅዱስ እያነበበ ነበር ስኩን ስጨርስ አንድ ነገር አልኩት ይህ መጸሐፍ ግን እደተበረዘ ታውቃለህ ብዬ ጠየኩት ዴቪድም መጽሐፍ ቅዱሱን ዘጋና ቀጥል ልስማህ አለኝ ይህ ለእኔ የእረፍ ምልክት መሆን ነበረበት፤ ቀጠልኩ በመጀመሪያ የምታነበው እንግሊዘኛ ነው ኢየሱስ ደግሞ እንግሊዘኛ አልተናገረም እርሱ የተናገረው አርማይክ ነው፣ የመጀመሪያው ቤተክርስቲያንም አርማይክ ነበረች ስለዚህም ሒብሪው ነው የተናገሩት አዲስ ኪዳንም በተጻፈበት ወቅት ግሪክ ተናጋሪዎች ብዙ ስለነበሩ የተጻፈውም በግሪክ ነው ክርስቶስ የተናገረው አንተ ጋር በደረሰ ግዜም የትርጉም ትርጉም ነው ታዲያ በትርጉም ሒደት ምንም የተሳሳታ እና የተረሳ ነገር የለም ልትለኝ ነው አልኩት፡፡ ከዛም ቤተክርስቲያን ለዘመናት መጸሐፍ ቅዱስን በላቲን ነበራት ይህም ሌላ ትርጉም ነበር ከዛም ወደ እንግሊዘኛ ከመተርጎሙ በፊት ጀርመንኛ ነበር ስለዚህም አንተ ያለህ የትርጉም ትርጉም ትርጉም ትርጉም ትርጉም ትርጉም ነው አልኩት ስለዚህም ነው ደግሞ ብዙ የእንግሊዘኛ ትርጉም መጸሐፎች ያሏቹ ታዲያ ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ በምን አውቃለሁ አልኩት፡፡ይህን ለብዙ አማኞች ብዙ ግዜ ሞግቼበታለሁ ማንም ይህን ሊያስረዳኝ አልቻለም ነበር፡፡ እርሱ ግን ነቢል አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ አለኝ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ከእናትህ ጋር ስታወራ ሰምቼሃለው በእንግሊዘኛ ነበር ምታወራለው አለኝ አይደለም አልኩት እርሷን ምን እንዳወራኃት የነገርከኝ ግን በእንግሊዘኛ ነው የተሳሳተ ትርጉም ነበር? አለኝ አይደለም አልኩት አየህ ነቢል አንተ ከአንድ በላይ ቋንቋ ተናጋሪ ነህ በአንድ ቋንቋ የሰማኸውን በሌላ ቋንቋ በትክክል ተረጉመህ መናገር ትችላለህ በዚህም መልዕክቱ አይሳሳትም ፡፡ የእኛም እምነት አባቶች ያደረጉት ይህንኑ ነው አለኝ፡፡ ክርስቶስ ምንም ቋንቋ ይናገር ምንም ያንን ወደ ግሪክ ከእነዚያም የመጀመሪያ ቅዲዎች ዛሬ ከ5500 በላይ ጥንታዊ ጽሑፎች በእጃችን አሉ በዚህም ጥናታዊው የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ምን እንደሚል እናውቃለን ይህ ብቻ አይደለም እነዚያን ሁሉ የግሪክ ጥንታዊ ጽሑፎች ብናጣቸው እንኳ ከ10,000 በላይ ላቲን፣ ሲሪያክ እና ኮፕቲክ የአዲስ ኪዳን የትርጉሞች አሉን አጠቃለይ መጸሐፉን ከእንደገና መልሰን ልናደራጀው እንችላለን፣ ይሁ ሁሉ ባይኖረን እንኳ ከመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን አባቶች የተጠቀሱ ከ30,000 በላይ ጥቅሶች አሉን በዚህም የመጀመሪያው የአዲስ ኪዳን መልዕክታት ምን እንደሚመስሉ እናውቃለን አለኝ ፤ ተመለከትኩትና ዴቪዲ በጣም ብዙ አማኞችን አናግሬያለው ማንም አሁን አንተ ያልከኝ ብሎኝ አያውቅም አልኩት እርሱም መልሶ እዋሸውክ መሰለህ አለኝ እኔም አዎ አልኩት በዚህ እኔና ዴቪድ ጓደኛሞች ሆንን ፡፡

ለሚቀጥሉት ግዜያትም አብረን ክርስትናን በሁሉም መልክ ፈተሸነው፣ ጥናቶችን መመልከት፣ ጥንታዊ ጽሑፎችን ማንበብ ተያያዝን ከዚያም መጸሐፍ ቅዱስ አለመበረዙን እና አለመሳሳቱን የሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎች አገኘሁ፡፡ ከአመት በኃል እሺ መጸሀፍ ቅዱስ አለመበረዙን እና አለመሳሳቱን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን አግኝቻለው አለኩት፡፡ ነግር ግን በቅዱስ ቃሉ ውስጥ ክርስቶስ የቱ ጋር ነው አምላክ ነኝ የሚለው ብዬ ጠየኩት ለእኔ እርሱ በጣም ወሳኝ ነውና፣ የክርስትና ዋና ቁልፍስ ምንድን ነው? ክርስትናን እውነት ሚያደርገው ምንድነው? የሚለውን ጥያቄዎች አነሳው በዚህ ስለ ሞቱ፣ ትንሳኤው፣ እና አምላክነቱን መልስ ለማግኘት ፍለጋ ጀመርን በዚህ ግዜም ለኔ እነዚህ ወሳኝ እውነቶችና እምነት ሚመሰረትባቸው ቁልፍ ጉዳዬች ናቸው፡፡ ከታሪክ አንጻር ፣ ከመጸሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉ ብዙ ማስረጃዎችን እና ምስክርነቶችን፣ ጥንታዊ የቤተክርስቲያን ጽሑፎችን ማገላበጥ ያዝን ከአመታት በኃላም ስለክርስትና እውነትነት ብዙ ጠንካራ ማስረጃዎች እንዳሉ ተረዳው፡፡ ስለሞቱ በታሪክ አልስማማ እስካላላልን ድረስ ታሪክ ሁሉ ክርስቶስ እንደሞተ በአንድነት ይስማማል፣ ስለትንሳኤው ያገኘናቸውም ማስረጃዎች ሁሉ የሚወስዱን የመጨረሻው ድምዳሜ ኢየሱስ ከሞት እንደተነሳ ነው፣ ስለ ጌትነቱም ቢሆን ለረጅም ግዜ ከመጸሐፍ ቅዱስ የጠቀስኳቸው ጥቅሶች እኔ ከአውድ ውጪ ስናገራቸው የነበርኩት በዩሐ 1:1 እና 14 ላይ ያሉትን ተመለከትኩ አምላክ ስጋ ሆነ ይላል በርግጥ ክርስቶስ አምላክ ነበር እያለኝ ነው፡፡ በዚህም ስለ ክርስትና ያሉ ማስረጋዎች እጅግ ተአማኒ እና ጠንካራ እንደሆኑ አስተዋልኩ ከዛም ዴቪድ ነቢል እንግዴ ክርስትናን ላለፉት ሶስት አመት ስንፈትሽ፣ ስንገመግም ነበር ከአንድ እስከ መቶ፣ መቶም ልክ ነው በሚል ውጤቱን ምን ጋር ታስቀምጠዋለክ አለኝ እኔም ከሰማኒያ እስከ ሰማኒያ አምስት አልኩት ታዲያ እስካሁን ለምን ሙስሊም ነህ አለኝ? እኔም ምክኒያቱም እስልምና መቶ ላይ ስለሚገኝ አልኩት እርሱም ነቢል ለምንድን ነው ክርስትናን ለማጥናት እና በማስረጃ ለመፈተሽ እንደሄድነው እስልምናን በዚህ ልክ ማታየውና ማትፈትሸው አለኝ ቀላል ሙግት ባይሆንም ተቀበልኩት፡፡ነገሩ እንዲህ ነው ክርስትናን በጣም በጥልቀጥ እና ከብዙ ነገሮች አንጻር ነው የፈተሸኩት፣ እውነታው ጋር ለመድረስ የጣርኩት ያንን ማድረጌ ደግሞ ለዴቪድ ሙግት ተጋላጭ አድርጎኝ ነበር፤ በዚያ መለኪያ እስልምናን ስመለከተው ግን ድምጥማጡን ነበር ያጠፋው የእስልምናን እውነት እና ልክነት የሚያሳዩት ማስረጃዎች ስለክርስትና ካገኘነው ጋር ሲነጻጸር ምንም አይገናኝም ነበር፡፡

በዚህ በጣም ግራ ገብቶኝ አለሜ ሁሉ ተቃውሶብኝ ነበር። ጉዳዩ በእነዚህ ምክኒያቶች ነው እስልምናን መከተል ያለብህ ብዬ ማሳያቸው እውነቶች ማግኘት አለመቻሌ ብቻ ሳይሆን ዴቪድ በእስልምና ላለማመን ምክኒያት የሚሆኑ ብዙ እውነቶችን ያሳየኝም ስለነበር እንዳንዶቹን እውነቶች እኔም እንኳ ሰማቻቸው እና አስተውያቸው ማላውቃቸው ስለ ነበሩ ነው። እነሱን በጥለቀት ለማየት በሞክርኩ ልክ እርሱም ብዙ ጥያቄዎችን እና ሙግቶችን ይጨምርልኝ ነበር አብዛኞቹን ይህ ወሳኝ ጉዳይ አይደለም እያልኩ እተወው ነበር ግን ከመቶ በላይ ሙግቶችን አቀረበብኝ ይህም አለሜን በሙሉ ለወጠው በዙሪያዬ በሙሉ ሙስሊሞች አሉ፣ ቤተሰቦቼ ሙስሊሞች ናቸው፣ አያቴ እና ቅድመ አያቶቼ ህይወታቸው ያለፈው ኢስላምን ሲሰብኩ ነው። ያገኘዋቸው ማስረጃዎች ቀላል አይደሉም ይህን ዝምብዬ ለቤተሰቦቼ መናገርም አልችልም ነበር። በዚያን ግዜ ወደ ፈጣሪ ማን ነህ እያልኩ መጸለይ ጀመርኩ፣ አላህ አንተ የኢስላሙ አላህ ከሆንክም ሆነ ኢየሱስ ከሆንክ ባክህ አስታውቀኝ ማለት ጀመርኩ ፍለጋዬ ከዚያች ቀን ጀምሮ ማስረጃዎችን አገላብጦ እውነትን ከመፈለግ ወደ ልብ ፍለጋ ተለወጠ። በቀን ውስጥ ያሉትን አምስት ጸሎቶች እየጸለይኩ በጣም አለቅሳለሁ ማን ነህ አንተ የሚለው ጩኸቴ ነው፣ ሙስሊሞች ፈጣሪ በህልም እና ራዕይ እንዲናገራቸው ይጠይቃሉ ይህ የሆነበት ደግሞ ከፈጣሪ ለመስማት ስለማይጠብቁ ነው እርግጥ ነው ክርስቲያኞች መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ አለ ብለን ስለምናምን ከእርሱ ለመስማት አምነት አለን በእስለም ግን ይህ በጣም ከባድ ነው አላህ ይናገራል ተብሎ የሚታሰበው ለነቢያት ነው እርሱንም በመላዕክት በኩል እንጂ በቀጥታ አያናግራቸውም፤ አንተ ማን ነህ ከፈጣሪ ለመስማት የምትጠብቀው!! በህልም እና በራዕይ ካልሆነ በስተቀር ነው አስተሳሳበቻን። ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲናገረኝ ስጠይ በህልም በራዕይ ነው ጥናቶችም እንደሚያሳዩት አሜሪካን ውስጥ ከእስልምና ወደ ክርስትና የመጡ ሰዎች 60% በህልም እና በራዕይ ነው ይህ ቁጥር በአለም ሁሉ ተመሳሳይ ነው። እግዚአብሔርም ራዕይ እና ሶስት ህልሞችን አሳየኝ በዚህም መንገድ ይመራኝ ጀመር። ይህን ምሪትም እያገኘው እንኳ ብዙ አሳቦች ወደ እኔ ይመጡ ጀመር ምናልባት የሚያሳየኝ እግዚአብሔር አይደለም ሰይጣን ሊሆን ይችላል የሚሉ ሀሳቦች ይረብሹኛል።

በውጤም ደግሞ ክርስቶስን ለመካድ በቂ የሆነ አቅም እንደሌለ አውቃለሁ በዚህ ሁኔታ ትምህርት ቤት እየሄድኩ አለቅስ ነበር እግዚአብሔር ሆይ ማድረግ ያለብኝን አውቃለሁ ግን ትንሽ ግዜ ስጠኝ እል ነበር ምክኒያቱም በእኔም ሆነ በቤተሰቤ ላይ የሚመጣውን አውቅ ነበርና ፤ የዚያ ቀን ወደ ትምህርት ቤት ከመሄድ ወደ ቤቴ ተመለስኩ በብዙ ጭንቀት፣ ለቅሶ እና ግራ መጋባት ውስጥ ሆኜ መጸሐፍ ቅዱሴን እና ቁርአኑን አውጥቼ እግዜአብሔር ሆይ ማጽናናትህን እፈልጋለሁ አልኩት ቁርአኑንም ገልጬ በህይወቴ ለመጀመሪያ ግዜ ለመጽናናት የሚሆን ቃል መፈለግ ጀመርኩ ገጾች ማገላበጥ ያዝኩ ነገር ግን የተጨነቀን፣ ግራ የገባውን ሰው ሊያጽናና የሚችል ቃል ላገኝበት አልቻልኩም እንድስኳ! ይህ መጸሐፍ ለኔ አይሆንም ብዬ ወደጎን አደረኩና መጸሐፍ ቅዱሱን ደግሞ አነሳው ከዚህ ቀደም መጸሐፍ ቅዱሱን ለመጽናኛ ቃል ፍለጋ ከፍቼው አላውቅም እውነት አለመሆኑን ለማረጋገጥ እና ለመተቸት እንጂ ከዛም ከየት ልጀምር ብዬ አዲስ ኪዳን ማቴዎስ ወንጌል ላይ ከፈትኩ መጀመሪያ ላይ ብዙ ስሞች እና ዘር ሃረግ ነበር እርሱን አለፍኩት ማንበቡ ቀጠልኩ ምዕራፍ አምስት ጋር ለመድረስ ብዙ አልፈጀብኝም እዚያ ላይ ህይወቴን የሚቀይር ቃል አገኘው የሚያዝኑ ብጹዓን ናቸው ይጽናናሉና ይላል እነዚያ ቃላት ከወረቀቱ ዘለው ልቤ ውስጥ የገቡ ያህል ይሰማኝ ጀመር፣ ኢየሱስ ከሁለት ሺ አመት በፊት ለኔ የተናገራቸው እስኪመስለኝ ድረስ ተሰማኝ መጸሐፍ ቅዱስን ከቀኝ ወደ ግራ እያደረኩ አነብ ጀመር ዴቪድ የሰጠኝ መጸሐፍ ቅዱስ ደግሞ ለማጥናት ጥሩ ነበርና ከስሩ የተጻፉ ማጣቀሻዎች ነበሩት ጥያቄዎችን ሳነሳ መልሶቹም አብረው ነበሩ። ካዛ ግን ማቴዎች አስር ላይ ደረስኩ እንደዚህም የሚል ቃል አነበብኩ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ ፤ በሰውም ፊት ለሚክደኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው አባቴ ፊት እክደዋለው፤ ይህ ለእኔ ግልጽነበር በእርሱ ለማመን ሚያስፈልገው ሁሉ ማስረጃ ነበረኝ፣ መንፈሳዊ እርዳታንም እየሰጠኝ ነው የቀረው ነገር እኔ ስለእርሱ አለመመስከሬ ነበር።

እግዚአብሔር ሆይ ይህን ካደረኩ ግን ቤተሰቤን መተው አለብኝ አልኩ እዛው ክፍል ላይ ቀጣዬቹ ቃሎች ምን እንደሚል ታውቃለችሁ በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላቹ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም ወረድም ብሎ ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም ፣ ይህን እዛው ላይ እያነበብኩ ጌታ ሆይ ቤተሰቦቼን ብቻ አይደለም ሙሉ ህይወቴን መተው አለብኙ እያልኩ ቀጣዩ ቁጥር እንዲህ ይላል መስቀሉን የማይዝ በኃላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም። ህይወትህን ያስከፍላል በዚያን ወቅት ክርስቶስን ለመቀበል ጸለይኩ በዚህ ጸሎት ያገዘኝ አልነበረምና የሙስሊም ጸሎት ይመስል ነበር ግን እንዲህ አልኩ እየሱስ አንተ ጌታዬ እንደሆንክ አምናለሁ ልከተልህ ፈልጋለው፣ በመስቀል ስለሞትክልኝ ከሞትም ስለተነሳህ ወደ ሰማይም መግባት ስለሆነልኝ አመሰግናለሁ ይህ ነበር ጸሎቴ። ከዛም ወንጌላትን በጣም ማጥናት ጀመርኩ ግን ያ ተቀይሮ ወንጌሉ እኔን ከአቅም በላይ ሲይዘኝ ቤተሰቦቼ አወቁ ያም ለኔ በጣም በህይወቴ የተሰበርኩበት ቀን ነበር እናቴን በጣም እወዳት ነበር እርሷም ተመለከተችኝና በምልከታዋ ውስጥ ግን እንዴት ትክደኛለህ የሚል እይታ አየችኝ ፣ አባቴም ነቢል ዛሬ ከጀርባዬ አከርካሪ አጥንቴ እንደተነቀለ ተሰማኝ አለኝ ይህን ብቻ ነበር የተናገረው ። በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ ጸለይኩ ለምን አልገደልከኝም? አንተን እንዳመንኩህ ገድለኸኝ ቢሆን ኖሮ እኮ እኔም መንግስተሰማይ እገባለሁ፣ ቤተሰቦቼም በእኔ ልባቸው አይሰበርም ነበር እያልኩ ማልቀስ ጀመርኩ፤ በዚያ ቅጽበት እግዚአብሔር በድምፅ ማጉያ የተናገረኝ ያህል ድምጽ ሰማሁ "ጉዳዩ ስለአንተ አይደለምም አለኝ " ማልቀስ አቆምኩ ከዛም ወደ ውጭ ወጣሁ ሁሉም ነገር አዲስ ሆኖ ታየኝ ቀድሞ ምኖርበት ቤት፣ ሰፈር ነው ነገር ግን ሁሉም አዲስ ሆኖ ይሰማኝ ጀመር፤ በመንገድም ላይ አንድ ሰው እየተራመደ አየው ለእኔ ግን አምላክ ሊሞትለት የወሰነለት ሰው ሆነ ታየኝ፤ በሙስሊም እይታ ፈጣሪ ከላይ ሆኖ ይገዛል ከሰዎችም ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ፣ አባታቸውም አይደለም በምንም ሁኔታ፣ እኔ ደግሞ በዚያ ቅጽበት እግዚአብሔር ማን እንደሆነ አስተውያለው እርሱ የአለማት ፈጣሪነው፣ የፍጥረት ሁሉ አምላክ ፣ ይህን ያህል ነው ሃያልነቱ ነገር ግን ደግሞ ወደ ምድር ለመምጣት የፈቀደ፣ ከሰው የተወለደ፣ አሰቃቂ የሚባል መከራንም የተቀበለ፣ በእጆቹ የሰራ፣ እንደኛ የሆነ ሆነ አስደናቂው ይህን ስለ ፈጣሪ ነው የምናወራው ለምንድን ነው እንዲህ የሚያደርገው ወይም ምን አስገድዶት ነው። ለዚህ ሁሉ ምላሹ ግን እኛን ይወደናል ነው መውደዱም ደግሞ በዚያን ያህል ነው። ይህ ነው ወንጌሉ ይህ ነው የእኔ አምላክ !!

በዚህ መልኩ ጌታ ኢየሱስን የተገናኘው ዶ/ር ነቢል ቁረሺ በእቅብተ እምነት፣ በወንጌል ሰባኪነት እና ጸሐፊነት ከአምለኩ ጋር ለመሆን እስካንቀላፋበባት ቀን ድረስ በታማኝነት ሩጫውን ሮጧል። Seeking Allah finding Jesus, No God But one እና Answering Jihad የተሰኙ መጸሐፎችን ጽፏል ። በራቪ ዘካርያስ የወንገል አገልግሎት ውስጥ በነበረው ቆይታ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች እና ተቋማት በክርስትና እና እስልምና ዙሪያ የእቅብተ ዕምነት አገልግሎትን በማድረግ ሰፊ ግዜውን አሳልፏል፣ በብዙ ቤተክርስቲያኖች የወንጌል ትምህርትንም በብዙ ይሰጥ ነበር ዶ/ር ነቢል በአገልግሎቱ በአስራ አንድ ዓመት በቀጥታ ከ40,000 በላይ ሙስሊሞች ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንደተጨመሩ ይነገራል ከዚህም ባለፈ በተዘዋዋሪም ሆነ በመጸሐፎቹ በተለይም Seeking Allah finding Jesus በሚለው የህይወት ምስክርነቱን በሰፊው በሰጠበት መጸሐፉ ከ 75,000 በላይ ሙስሊሞች ፣ ኤቲይስቶች እና ሎች ም ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲጨመሪ ምክኒያት እንደሆነ ይነገራል። ዶ/ር ነቢል 2016 ዓ.ም በመጨረሻው ከካንሰር ጋር እየታገለ ባደረገው የመድረክ አግልግሎቱ አስተምሮት ሆነ ከዚያ ቀደም ሰብኮት የማያውቀውን ዩሐንስ 3:16 አስተማረ ካለበት ህመም በላይ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ አለምን የወደደበትን ያንን ፍቅር አድምቆ ሰበከ በስብከቱም ኢየሱስ የወሰደው የውልጆች መከራ የሚገባው እንዳይደል ግን ስለወደዳቸው በወደዳቸው የከፈለው ዋጋ መሆኑን አስተማረ። ነቢል በዚህ ቀን እንዲህ አለ በእኔ ሊመጣ ሚችለው ከባዱ ነገር ሞት ነው ሞትም ቢሆን ግን ክርስቶስ ከወሰደው ከሰው ልጆች መከራ ጋር እስመጨረሻውም በጨከነበት እኛን የማዳን ስራ ጋር አይስተካከልምና በኔ ሞት ክብሩን ከገለጠ አይደለም አንዴ ደግሜም ልሙት ያለገለገልኩት፣ የሰበኩት ጌታ አልፈሰኝም ብዬ የአመታት እምነቴን አልቀይርም ስብከቴን አልሽረሽርም ፣ ሞት የነገሮች ማብቂያ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ሒወት መጀመሪያ ነው ይህን እኔ መሰክራለው የነቢል መልዕክት ማብቂያ ነበር ።

ዶ/ር ነቢል ቁረሺ ዛሬ በህይወት የለም በትንሳኤ ቀን እንደምንገናኝ እኛም እንደምናየው አምናለሁ፡፡ ስራዎቹ እናትምህርቶቹ ግን ህያው ናቸው ዛሬ ዩቲዩብ ቻናሎቹን ጎበኘው ብዙ ሚሊየን ተመልካች ያላቸው ናቸው አማዞን የኦንላይን የመጸሐፍት መሸጫ ውስጥ ምርጥ መቶ ብሎ ከያዛቸው ውስጥ የዶ/ር ነቢል መጸሐፎች ይገኙበታል፣ ኒው ዬርክታይምስ በወቅቱ ከፍተኛ ሽያጭ ካስገኙ ክርስቲያናዊ መጸሐፍት በታሪኩ ቀዳሚ አድርጎ መዝግታል፡፡ ዛሬ እርሱ የጀመረው እቅበተ ዕምነት እና ብዙዎችን ወደ ወንጌሉ የመጥራት ጉዞ በትዳር አጋሩ ሚሼል ቁረሺ ቀጥሏል እግዚዘብሔር እንዲረዳት ለብዙዎች መዳን እንዲያደርጋት ለልጇም ጀያ የአባትን ፍቅር ሳትጠግብ በሁለት ዓመቷ የተለያት አባቷን ፍቅር መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጣት የጸሎት ርዕሳቹ እየለመንኩ፡፡ ዶ/ር ነቢል ቁረሺን የመሰሉ የወንጌል አርበኞች ለብዜዎች ብርሃን የሚሆኑትን እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን፣ ለምድሬ ኢትዬጵያ እና ለዓለም እንዲያስነሳ እንዲያበዛም መሻቴም ነው ፡፡ ይህን ያነበብን ራሳችንን ለማየት ከሆነልን ፣ የወንጌል መልእክተኛነትን ህይወት ከዛም ስራ እንደገና እንድናስብ ከቻል መልካም ነው ፡፡ የተለመደ ባይሆንም ግን እንዲህ ልመርቃችሁ እና ላብቃ እናንተ ያላችሁትን ሳይሆን እግዚያብሔር ያለውን መኖር ይሁንላችሁ፤ እናንተ ለመያዝ ከምትታገሉት በላይ እርሱ የያዘላችሁን ኑሩ!!

አማኑኤል ገዛኸኝ

# ምስክርነት

ዶ/ር ነቢል ነቢል የወንጌላውያን ማህበረሰብ ውስጥ ብቻ ሳይሆን እርሱ ራሱ ወንጌላዊም ነበር፡፡ አለምን በወንጌል ለመድረስ የነበረው ጥማት ጥልቅ ነበር ፡፡እኔ በግልጽ ጥልቅ ተሃብ፣ መሰጠት እና ጥሪም የነበረው አገልጋይን በርሱ ውስጥ ተመልክቻለው ፕሮግራም ታዳሚዎቻችንን እና ተካፋዬቻችን አፍ አስከፍቶ ማውራት ይችል ነበር፡፡
ወደ ራቪ ኢንተርናሽናል እንዲመጣ ስጋብዘው እርሱም እኔም አንድ ቅድመ ሁኔታ አስቀመጥን፡፡ የእርሱ ቅድመ ሁኔታ ከእኔ ጋር አንድ አመት እተጓዘ ልምድ መቅሰምን ነበር፣ እኔ ደግሞ ከዚህ አንድ አመት በኃላ ወደ ኦክስፎርድ እንዲሄድ አልኩት ምክኒያቱም ዶክትሬቱን መጨረስ ነበረበት ለቀጣዩ አገልግሎት በይበልጥ ይዘጋጅ ዘንድ ነው፡፡ እርሱም ያንን ተስማማ፡፡ አጎቴ እያለ ይጠራኝ ነበር፤ የቡድናችን አባልም ሆነ፡፡ በሄደበት ቦታ ሁሉ ሰዎች ተመልሶ እንዲመጣ ይጠይቁታል፡፡ ከእኛንዳንዱ ፕሮግራሞች በኃላ ለምግብ ስንቀመጥ አጎቴ እንዴት ነበርኩ ብሎይጠይቀኛል ፡፡
የካንሰር ታማሚ እንደሆ ከታወቀ በኃላ ሜይ ወር ላይ አጎቴ አንድ ጉዞን ካንተ ጋር ላድር አለኝ ዶክተሮችክ ከፈቀድ እሺ አልኩት፡፡ ወደ ማሌዢያም ይዜው ሄድኩ ፡፡ ሰውነቱ ደክሞ ነበር መንፈሱ ፣ ንግግሩ ግን በጣም ሃይለኛ ነበር ያስተላለፈው መልዕክት የዛች ቀን ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግስት ጨመረች ፡፡ ለሰዎች ጥያቄ የሚመልሰው መልስ ጥልቅ እና ግልጽ ነበር ፡፡ ከእያንዳንዱ ምላሽ በኃላ ብዙ ጭብጨባ ይከተለዋል ፡፡ ለብቻ መጥተው ሲጠይቁጥ ይመልሳል፣ ጸልይልንም ሲሉት ይጸልያል፡፡ ለመመልከት አስደናቂ ነበር እርሱ ዶ/ር ነቢል ቁረሺ ነው የወንጌሉ አርበኛ፡፡

**ዶ/ር ራቪ ዘካሪያስ ስለ ነቢል ካሰፈሩት ማስታወሻ የተወጠጣጣ**

# ሚስዮናዊነት እና የበሽታ ወረርሽኝ

ሁልጊዜም እንደምለው ደግሞም እንዳማምንበት ሚስዮናዊነት የከበረ ጥሪ ነው። ይህ የከበረ ጥሪ ታዲያ ልክ እንደወርቅ በበዙ ነገሮች ይፈተናል። የሚስዮናውያንን ተግዳሮቶች መዘርዘር ብጀምር መጨረሻ የለኝም።
ከተፈጥሮው እስከ ሰው አመጣሽ ተግዳሮቶች በየቦታው የተሰማሩ ባህል ዘለል ሚሰዮናውያንን ይፈትናሉ። በቅርቡ በአለማችን የተከሰተው የ ኮቪድ 19 ወረረሽኝ የሚሰዮናውያንን ተልዕኮ በእጅጉ እየፈተነ እንዳለ እረዳለሁ።
የሚስዮናውያንን ተግዳሮቶች ሰው አመጣሽ እና የተፈጥሮ ብለን ልንከፍላቸው እንችላለን። ሰው አመጣሾቹን ደግሞ የውስጥ እና የውጭ ብለን ልናያቸው እንችላለን። የውስጥ ሰው ሰራሽ ተግዳሮቶች ከላኪ ቤተክርስቲያን/ድርጅት የሚቀርብ እርዳታ እና ክትትል ማነስ እስከ ሚስዮናዊው የመንፈሳዊ ሕይወት መሰናክሎች ይደርሳሉ። ከውጭ የሚመጡት ጫናዎች ደግሞ ሚስዮናውያኑ በተሰማሩበት አከባቢ ባሉ ሕዝቦች/መንግስት ሚስዮናውያኑ ላይ የሚደርሱ ጫናዎች ናቸው። የተፈጥሮ ተግዳሮቶችንም በዚህ መልኩ ለሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን። አንደኛው በዘር የሚመጡ ሲሆኑ ሌሎቹ በጊዜ ሂደት የሚከሰቱ ናቸው። በዘር ወይንም ከውልደት የሚመጡ ተግዳሮቶች መካከል የሚስዮናዊወ በተፈጥሮ የሚመጣ አካል መጉደል ዋነኛው ነው። አካል ጉዳተኛ ሆነው ሚስዮናዊ ለመሆን የወሰኑ ብዙ ሚስዮናውያን በታሪክ ነበሩ አሁንም አሉ። ከዚህ ባለፈ በጊዜ ሂደት ከሚመጡ የተፈጥሮ ተግዳሮቶች መካከል በሽታ ፣ የተፈጥሮ አደጋ እንደ መሬት መንቀጥቀጥ ፣ ጎርፍ ፣ ድርቅ ወዘተ ያሉት ይገኙበታል። ኮቪድ 19 የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝም እዚሁ መሃል ይመደባል። የኮሮና ቫይረስ እና የሚስዮናውያኑ ጉዳይ ያሳስበኝ የጀመረው ገና የቻይናዋ ዉሃን ከተማ ከቤት አትውጡ እንደተባሉ ነበር። ሚስዮናውያን ወረርሽኙን አስመልክተው እንዴት ምላሽ ይሰጣሉ የሚለው በጊዜው አሳስቦኝ በጊዜው ያንዳንድ ሚስዮናውያን ሁኔታን ሳጣራ ነበር።በጊዜው በኮቪድ 19 ከተጎዳችው ከቻይናዋ ዉሃን ከተማ የሆነ ስሙ እንዲጠቀስ ያልፈለገ አንድ ሚስዮናዊ ለላከው ድርጅት የፃፈውን ደብዳቤ አንብቤ ተገርሜያለው ደግሞም ተደስቻለሁ። ሚስዮናዊው «እኛን የሚያሳስበን የቫይረሱ በፍጥነት መዛመት ሳይሆን እኛ እንዴት የአምላክን ፍቅር በፍጥነት እናዛምታለን የሚለው ነው» የሚለው አባባሉ ደግሞ እጅግ የሚያበረታታ ነበር። እንደዚህ ብርቱ ሚስዮናውያን ቁጥራቸው ብዙ ነው። ሆኖም ግን ይህ ወረርሽኝ ስጋት ላይ የጣላቸው፣ ጥያቄ የፈጠረባቸው እና ግራ መጋባት ውስጥ የከተታቸው ሚስዮናውያንም እንዳሉ እሙን ነው። በዚህም ምክንያት ወደ ሀገራቸው የተመለሱ ሚስዮናውያን እንዳሉ አንብብያለሁ።
አብዛኞቹ ሚስዮናውን በተላኩበት አካባቢ በመቆየት እና በመመለስ ሃሳብ ውስጥ እንደሚገቡም አስባለሁ።
ስለዚህም ከዚህ እንደሚከተለው ስለ ሚስዮናዊነት እና በሽታን በተመለከተ ጥቂት ነጥቦችን እንይ ከዚያም የሚስዮናውያንን ድርሻ በወረርሽኝ እና በተፈጥሮ አደጋ ወቅት አይተን እንጨርሳለን።

## ሚስዮናዊነት እና በሽታ

ሚስዮናዊነት እና በሽታን በተመለከተ በዙ ነጥቦችን ማንሳት ይቻላል። ለዚህች አጭር ፅሁፍ ሚስዮናዊነት እና በሽታ መካከል ያለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ታሪካው እይታ እንዲህ አስቀምጬዋለሁ።
በመጀመሪያ የሚስዮናዊነት ትልቁ ምሳሌ መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ተልዕኮውን አስመልክቶ ሲናገር «የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው… ለታሰሩት መፈታትን ለታወሩት ማየትን እንድሰብክ ልኮኛል» (ሉቃ 4:18) ብሏል። በሚስዮናዊነት እና በህመም መካከል ያለው ግንኙነት እዚህ ጋር ይጀምራል።
ክርስቲያናዊ ተልዕኮ በሕዝቦች ቁሳዊ ፣ አካላዊ እና መንፈሳዊ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው። ለዚህም ነው ስለ 10/40 መስኮት ለይተን የምናወራው። የሕዝቦች ፍላጎት (need) ከሆኑት ውስጥ ደግሞ ለአካላዊ በሽታ ፈውስ አንዱ ነው። አካላዊ በሽታ ትልቁ የሚስዮን ምክንያት ነው።

# የቀጠለ ....

በሽታ ባይኖር ብዙ ሚስዮን ባልኖረ ነበር። ስለዚህ በመጀመርያ ደረጃ ሚስዮናዊነት እና በሽታን ስናስብ ልንረዳው የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር ሚስዮናዊነትን እጅግ አስፈላጊ ነገር ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ እና ዋነኛው የበሽታ መኖር ነው። ታማሚዎችን የመድረስን አገልግሎት ጌታችን ኢየሱስም ቢሆን ሐዋርያቱ ችላ ያላሉት አገልግሎት ነው።በታሪክም የተደረጉ አሁንም እየተደረጉ ያሉ የሚስዮን እንቅስቃሴዎች ዘላቂ ውጥቴ ያስመዘገቢት በአብዛኞቹ በሕክምና የተደረጉ የሚስዮን እቅስቃሴዎች (Medical Missions) ናቸው።
ሁለተኛ ልናስተውል የሚገባን ነገር ቢኖር በሽታ ሚስዮናውያንን የሚጎዳ ነገር እንደሆነም ጭምር ነው። እድል ብቻ ሳይሆን ብዙ ጉዳት ይዞ የሚመጣም ነገር ነው። ብዙ ሚስዮናውያን በተላኩበት አካባቢ በተከሰተ የበሽታ ወረርሽኝ ሞተዋል እነሱም ብቻም ሳይሆኑ ልጆቻቸውንም ያጡ ብዙዎች ናቸው። በሽታን ያለበትን አካባቢ ለመድረስ በሚደረግ የተሰዉ ብዙዎች ናቸው። የ Women' Home Missionary Society of the Methodist Episcopal Church በ1909 የደረሰው አመታዊ የሚስዮናውያን ሪፖርት ላየ አንዲት ሚስዮናዊት እንዲህ ብላ ሪፖርተረ አድርጋለች: «ባለፈው አመት ሶስቱ ልጆቻችንን በመልካሙ እረኛ ጉያ ገብተዋል። ቲቢ ሁሉንም ወስዷቸዋል።» ይህ እንዴት የሚከብድ ሪፖርት እንደሆነ ሁላችንም እንረዳለን። ይህ የብዙ ሚስዮናውያን ታሪክ ነው።
ወደ ሃገራችን ስንመጣም በበሽታ ምክንያት ልጆቻቸውን ያጡ ብዙ ሚስዮናውያን ታሪክ እናገኛለን። ኦኔስሞስ ነሲብ የተረጎሙትን የአፋን ኦሮሞ መጽሐፍ ቅዱስ ለማሳተም ስዊድን በሄዱበት ወቅት ባለቤታቸው ምህረት ሃይሉ በወሊድ ወቅት በተገናኘ ኢንፌክሽን በምስዋ ሞታለች።
ከዚህም በተጨመሪ በሱዳን በኩል ወደ አቢሲኒያ ለመግባት ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት ለፍተኛ ትኩሳት ይዟቸው እንደነበር በዚህም ምክንያት ሞት አፋፍ ደርሰው እንደነበር እና ህመሙ ሲበረታባቸው ጊዜ ወደ ኤርትራ እንደተመለሱ ኦኔስሞስ ነሲብ በሪፖርታቸው አስታውቀዋል። ሚስዮናውያን በሽታን ለማከም ሲሄዱ በሽታ ደግሞ ሚስዮናውያንን እና ያላቸውን ነገር ሊየሳጣቸው እንደሚመጣ ታሪክ ይነግረናል።

ሶስተኛው ልናስተውለው የሚገባን ነገር ቢኖር ግን ሚስዮናዊነትን እና በሽታን ስናስብ ሁልጊዜም ታሪክ በጥሩ ጎን ብቻ እንደሚያነሳቸው ማሰብ የለብንም። በታሪክ ሚስዮናውያን አንዱ ከምንተችበት ምክንያት መካከል በሽታን ከቦታቦታ በተለይም ወደ ሐገር በቀል ('Indigenous' ለሚለው ቃል አቻ ትርጉም ነው። እኔ በበኩሌ 'ሐገር በቀል' ከሚለው ይልቅ 'ጥሬ' የሚለው ቃል ያስማማኛል) ሕዝቦች ያዛምታሉ የሚለው ክስ ነው። ይህም ክስ እውነታነት እንዳለው ልንረዳ ይገባል። ለምሳሌ ወደ መጀመርያዎቹ አላስካ የሰፋሪዎች (Native Alaska dwellers) ጋር የተላኩ ሚስዮናውያን የቲቢን በሽታ እነዚህ ሕዝቦች ጋር አዛምተዋል የሚል ታሪካዊ ክስ አለ። ይህም ሐገር በቀል ሕዝቦች ለብዙ በሽታ ተጋላጭ ስላልነበሩ የሰውነታቸው በሽታን የመከላከል አቅማቸው ደካም ነው ወይም ሰውነታቸው ለመከመላከያ የሚሆኑ antibodies ማምረት አልጀመረም በሽታውን ከዚያ በፊት ስለማያውቀው። ታዲያ ሚስዮናውያኑ ወደ ሃገር በቀል ባህል በሚሄዱበት ጊዜ አብረው በሽታን ሊያዛምቱ ይችላሉ። ይህ ሶስተኛው በሚስዮናዊነት እና በበሽታ ዙርያ ልንረዳ የሚገባን እውነታ ነው። እንግዲህ ከዚህ በመነሳት ነው የሚስዮናውያነ ምላሽ ምን
መሆን አለበት የሚለውን ለመዳሰስ የምንሞክረው።

## የሚስዮናውያኑ ምላሽ በሽታን
## ሚስዮናውያን ምላሽ በሽታን በተመለከተ

እንግዲህ ከላይ ያጠቀስኳቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ተሪካዊ እውነታዎች እንዳሉ ሆነው። በእነዚህ እቅመታዎች መካከል ሚስዮናውያን በተለይም እጅግ ብዙ በሽታ ባለበት በ10/40 መስኮት የሚያገለግሉ ሚስዮናውያን እንዴት ማገልገል አለባቸው የሚለው ጥያቄ የሚነሳው። ለዚህ ጥቀያቄ ምላሽ ይሆናሉ ብዬ የማስባቸውን አራት ነጥቦች አንስቼ ፅሁፌን እቋጫለሁ።

# የጸሎት ጥሪ ለህዝብ ክፍሎች



# የአርጎባ ህዝብ ክፍል

**የህዝቡ ቋንቋ..........................................................አርጎቢኛ**
**አጠቃላይ የህዝብ ቁጥር...............................................192,000**
**ክርስትና ተከታዮች ከህዝቡ ሲሰላ .................................... 4.6%**
**የወንጌል አማኞች ከህዝቡ ሲሰላ................................... 1.40%**
**የተሰማሩ የቤተክርስቲያን ተካዮች....................................... አሉ**
**መፅሐፍ ቅዱስ በቋንቋቸዉ .......................... .................የለም**

የአርጎባ የህዝብ ክፍል አመጣጥ ላይ የተለያዩ ዓይነት አመለካከቶች ያሉ ቢሆንም ከስሙ ስያሜ እንደምንረዳዉ ከሆነ አረብ-ገባ ከሚል የሁለት ድርብ ቃላቶች ስያሜ የመጣ እንደሆነ ይታመናል። መገኛ ስፍራቸዉም በምዕራብ ይፋት ማዕከላዊ ኢትዮጲያ ይገኛሉ በተጨማሪም በስፋት በአማራ፣አፋር፣ኦሮሚያና ሀረሪ ክልል ይገኛሉ። ዋነኛ የህዝቡ መተዳደሪያ ግብርናና ሽመና ነዉ። በዚህ ህዝብ መካከል ጥቂት የሚባሉ ወንጌላዉያን አማኞች ይገኛሉ ነገር ግን ካለዉ የህብ ቁጥር ጋር ሲነፃፀር የምስራቹን ይዘዉ የሚሄዱ የወንጌል መልዕክተኞች ያስፈልጋሉ።

- ለዚህ ህዝብ የሚሄዱ ሚሲዬናውያን እንዲጨምሩ
- በዚህ ህዝብ መካከል ያሉ ጥቂት
- ሚሲዬናውያን እንዲደረዳ እና እንዲያግዝ
- እግዚአብሔር መለኮታዊ ጉብኝት ለዚህ ህዝብ እንዲያደርግ
- ስራቸው እንዲባረክ፣ የዘሩት እንዲበቅል፣ ዝናብ እንዳያጡ

ለዚህ ህዝብ እንድንጸልይ እጋብዛለሁ !

## 1) በእግዚአብሔር ተልዕኮ እንመን

የሚስዮናውያንነት ጥሪ የከበረ ነው። የመነጨውም ከአምላክ ከራሱ ነው። ጌታ ኢየሱስ ነው ታላቁ ሚስዮናዊ ከአብ የተላከ። እርሱ ደግሞ «አብን እኔን እንደላከኝ እኔም አረናነተን ልኬያችኋለሁ» ብሎናል (ዩሐ 20:21)። ይህ ጥሪ
የከበረ ነው የምንለው በዚህ ምክንያት ነው። በዚህ ጥሪ እናምናለን። አብ ኢየሱስን ሲልከው «ለታሰሩት መፈታትን ለታወሩትን ማየትን»
እንዲሰብክ ከሆነ። የእኛም ጥሪ ይኸው ነው። የተጠራነው ለታሰሩት መፈታትን ለታወሩት ደግሞ ማየትን ልንሰብክ ነው። በዚህ ጥሪ እናምናለን! በዚህ ጥሪ ማመናችን ደግሞ ወደ ተገፉት እና ወደ ታመሙት እንድንሄድ ያስገድደናል። በዚህ ጥሪ ማመናችን ወደ የተፈጥሮ አደጋ ወዳለበት ቦታ እንድንሄድ ያስገድደናል። ለሚስዮናዊው «ሕይወት ክርስቶስ ፤ ሞትም ጥቅም ነው»ና ምንመ ነገር ለመጋፈጥ
አይፈራም። ጌታ እንደላከው እርግጠኛ ይሁን እንጂ ጥሪውን ያከብራል።

## 2) ሚስዮናዊው ማህበረሰቡን ለመርዳት ዝግጁ መሆን አለበት!

ይህ ወሳኙ እርምጃ ነው። ወደ ታመመ፣ ወደ ተቸገረ ማህበረሰብ እግዚአብሔር ሲልከን ለዚያ አከባቢ የሚሆን ዝግጅት ያስፈልጋል። እዚህ ላይ ሁለት ቁልፈ ነገሮች አነሳለሁ።
የመጀመርያው ፀሎት ነው። «የፃዲቅ ሰው ፀሎት በስራዋ እጅግ ሃይልን ታደርጋለች» እንደሚል ቃሉ ከምንም ነገር በፊት እና በላይ ፀሎታችን ሃይል አለው። የታመመን ይፈውሳል! የሐዋርያቱም የመጀመርያ አማራጭ ፀሎት ነበር። «የምንሰጥህ ወርቅም ብርም የለንም በናዝሬቱ በኢየሱስ ስም...» ብለው በእምነት አባቶቻችን እንደተናገረ መርሳት የለብንም።
ሁለተኛው መርሳት የሌለብን ነገር ቢኖር ከፀሎት በተጨማሪ ሕክምናም ትልቅ ዋጋ እንዳለው ነው። ብዙዎቹ የሚስዮን እንቅስቃሴዎች ስር የሰደዱት እና መንግስታትን የተሻገሩት በሕክምና ስለተጀመሩ ነው። ለዚህም ነው ሁሉም ሚስዮናውያን የሕክምና ኮርስ (አጫጭርም ቢሆን ሙሉ) እንዲወስዱ የምመክረው።
ሀድሰን ታይለር ፣ ዊልያም ኬሪ ፣ ደፀቪድ ሊቪንግስተን ወዘተ የሕክምና ኮርስ ወስደው ነበር ወደ ሚስዮን አገልግሎት የተሰማሩት። ወደ ሀገራችን የመጡ ሚስዮናውያንም ዶ/ር ቶማስ ላምቤን ጨምሮ ሌሎችም ሕክምናን አጥንተዋል። አንድ ሚስዮናዊ በኢንጂነሪንግም ይመረቅ በሶሻል ሳይንስ መሰረታዊ የሕክምና እውቀት ሊኖረው ይገባል።
ድንገተኛ አደጋ ሲከሰት ማህበረሰቡን እንዴት መርዳት እንዳለበት ሊያውቅ ይገባል። ስለዚህም ሚስዮናውያን አጫጭር ኮርሶችን እንዲወስዱ አበረታታለሁ። በተለይ ድነገተኛ አደጋዎች ሲከሰቱ ለታማሚዎች ሊሰጡ የሚገባቸውን እንክብካቤዎች ማወቅ እጅግ አስፈላጊ ነው። ከዚህም ባለፈ ሙሉ ትምህርቱን የወሰዱ ደግሞ ክሊኒክ እና ሆስፒታል ለአከባቢው ምህበረሰብ መስራት ተልዕኳችንን እና ፍሬፀውን ዘላቂ ከማድረጉም በላይ በአከባቢው ሕዝብ ጥሩ እይታን ያሰጠናል።

## 3) ሚስዮናውያን መጠንቀቅ አለባቸው!

በሶስተኛው አለም ማለትም በ አፍሪካ እና
በኤስያ ከጥቂት ማህበረሰቦች በቀር በጫካ ተደብቆ (ከውጭ ህበረሰብ ጋር ሳይገናኝ) የሚኖር ህዝብ የለም። ስለዚህ ባህል ዘለል ሚስዮናውያን ወደ ሐገር በቀል ሕዝቦች በሽታን አዛምታለሁ የሚለው ስጋት ብዙም ሊገባቸው አይገባም። ሆንም ግን መጠንቀቅ ተገቢ ነው። ተላላፊ በሽታዎች እንደ ኮሮና ቫይረስ ያሉት አለምን እያካለሉ ያሉበት ጊዜ ላይ ሚሰዮናውያን እንቅስቃሴን መገደብ እና ከሚያገለግሉት ማህበረሰብ ጋር መተባበር ይኖርባቸዋል። ፍፁም ለችተኝነት ክፍተት መስጠት የለባቸውም ምክንያቱም የሚስዮን አገልግሎታቸውን በእጅጉ ስለሚጎዳ። ስለዚህ ሚስዮናውያን የወረርሽኝ ምክንያት እንዳይሆኑ አልፎም ደግሞ በቸልተኝነት የወረርሽኝ መስፋፋት ምክንያት እንዳይሆኑ ሊጠነቀቁ ያስፈልጋል።

## 4) በበሽታ ጊዜ የሚስዮናውያን ውሳኔ በጥበብ መሆን አለበት!

አስቀድሜ እንዳልኩት በወረርሽኝ ወይንም በበሽታ ጊዜ የሚስዮናውያን እና አብረዋቸው ያሉ የቤተሰቦቻቸው ጤና ሊናጋ ይችላል። ይህም ከባድ የውስኔ አጣብቂኝ ውስጥ ሚስዮናውያኑን ሊከት ይችላል። ዴቪድ ሊቪንግስተን አፍርካ ቆይታው ልጆቹን እና ሚስቱን በበሽታ ምክንያት በአፍሪካ መሬት ቀብሯል። ሃድሰን ታይለር በተመሳሳይ መልኩ በበሽታ ምክንያት ሚስቱን በቻይና ቀብሯል። እነዚህ ሁሉ ታዲያ ወደ ሃገር ቤት በመመለስ እና በመቅረት መካከል አጣብቂኝ ውስጥ ገብተው ነበር።
እንደ ኦኔስሞስ ነሲብ ያሉት ከሱዳን ወደ ኤርትራ ቤታቸው መመለስን መርጠዋል።

## የቀጠለ ....

ይህም አዋጥቷቸዋል ምክንያቱም አገግመው በጅቡቲ በኩል ወደ ኢትዮጵያ መግባት ስላስቻላቸው። እንደነ ዴቪድ ሊቪንግስተን ያሉት ደግመለ እዚያ ያሉበት የአፍሪካ መሬት ተቀበረዋል። ሚስዮናውያን በበሽታ ወቅት እንዲህ የውሳኔ አጣብቂኝ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ይህ ሊታወቅ ይገባዋል። ወደቤት ልመለስ ወይስ እዚሁ ልቅር የሚለው የውሳኔ አጣብቂኝ በጥበብ እና በፀሎት ሊደረግ ያስፈልገዋል። የእያንዳንዱ የበሽታ አነሳስ እና አካሄድ አንድ አይደለም እና ለዚህ ጉዳይ ቀመር ማውጣት አንችልም። ውሳኔው እያንዳንዱ ሚስዮናዊ ከእግዚአብሔር እና ከቤተሰቡ ጋር ተማክሮ የሚያደርገው ይሆናል።

በማጠቃልያ በዚህ የኮቪድ 19 ወረረሽኝ ወቅት በተከያዩ አከባበዎች ተሰማርተው ተልዕኮውን እየተወጡ ያሉ ሚስዮናውያን ልንፀልያላቸው

ደግሞም ላናበረታታቸው ያስፈልጋል። ልክ በቻይና የተሰማራው ሚስዮናዊ እንዳለው እየተዛመተ ካለው በሽታ ይልቅ የእግዚአብሔርነረ ፍቅር ማዛመት ግድ እንዲላቸው እንዲበረቱ የእግዚአብሔር ፀጋ ከሁላቸው ጋር ይሁን! አሜን!

**ናኦል በፍቃዱ**

**የወንጌል አገልጋይ፣ የስነመለኮት አስተማሪ፣ ጸሐፊ**

**እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህክምና ተማሪ**

# የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ እና የክርስቲያኖች ስደት

ኦፕን ዶር ዩ ኤስ ኤ የተባለ ተቋም በየአቱ በሚያወጣው የሃገራት እና የክርስቲያኖች ስደት ዝርዝር ውስጥ ቻይናን ለለፉት ረጅም አመታት ከመሰል ሀገሮች ጋር የፈት አውራሪ ደረጃዋን ሳታስደፍር እንደቆየች ነው፡፡ ምንም በቻይና መቶ ሚሊዬን አማኞች ቢኖሩም የሃገሪቱ መንግስት ከሚከተለው የኮሚንዝም ስርአት አንጻር ለብዙ ስደት ፣ እንግልት፣ እስር እና ሞትም ሲዳረጉ ኖረዋል አሁንም ይህ ታሪክ የተቀየረ አይደለም፡፡ የቤተክርስቲያን መዘጋት፣ መቃጠል፣ የአማኞች እና ቤተክርስቲያን መሪዎች መሰወር እና ወዳልታወቁ እስርቤቶች መወርወር የተለመዱ ዜናዎች ይመስላሉ፡፡

ዛሬም ድረስ በየቀኑ ወደነዚህ ወዳልታወቁ እስርቤቶች የሚወረወሩ አማኞች ቁጥር

እና የእስከዛሬዎቹ ሲሰሉ ብዙ መቶ ሲዎች የሚሆኑ አማኞች እስር፣ እንግልት ሲያልፍም የሞት ዳፋ ቀማሾች ሆነዋል፡፡ የቻይና የክርስትና ታሪክ የቅርብ እንዳይደል የታሪክን መዛግብት ማገላበጥ ብቻ በቂ ነው እነ ሮበርት ሞሪሰንን የመሰለ ሚሲየፐኖችን፣ በቅርብ እንኳ ሃድሰን ቴለር በተባለ ሚሲዬናዊ 1932 ዓ.ም የተጀመረው የሚሲዮን እንቅሳቃሴ ቻይና ኢን ላንድ ሚሽን በቻይና ለብዙዎች የምስራቹን ያደረሰ የወንጌል ንቅናቄ ነው፡፡



፱ አመት የተፈረደት ቻይናዊ ፓስተር እና ባለቤቱ



አማኞች ላይ የተበየን የሞት ፍርድ የተቃወሙ አማኖች ከመንገድ ሲታፈሱ

ይህ ብቻ ሳይሆን ቻይናውያ ሀገራቸውን ለመድረስ የሄዱበት የመከራ ግን የጽናት ታሪኮች ክርስትና ለቻይና የሃያኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ እንዳይደል ያሳየናል።

በማኦ ዜ ዶንግ ፊታውራሪነት የቻይና ህዝቦች በንግስት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 1949 ሲመሰረት ሀገረ መንግስቲ ሀይማኖት ጥቅም አልባ እና በቻይና እድል ፈንታ እንደለሌለው አሳወቀ ይህም በቻይና የነበሩ የምዕራባውያን ሚሲዬናውያንን ከሃገር እንዲወጡ የወንጌልን የማዳረስ ስራንም ሙሉ ለሙሉ መሸከም ያልቻለችን የቻይና ቤተክርስቲያንን ከማስተዳደር፣ የሚያስፈልገውን ግብዕት እና አቅም እስከመፍጠር ያለው ስራ ሁሉ በያኔዎቹ ቻናውያን የቤተክርስቲያን በሪዎች ላይ ወደቀ፤ ለቤተክርስቲያንም አስከፊውና ከባዱ ግዜ ይበል ጀመረ።

በዚህ ወቅት ሃገረ መንግስቱ በግዜው ለነበሩ የፕሮቴስታንት እና የካቶሊክ መሪዎች "ስሪ ሰፍ ፕትሪዮቲክ ሙቭመንት" የተሰኘ ቤተክርስቲያንን ከመንግስት ጋር የሚያጋባ ሰነድ ይዞ ቀረበበ በሰነዱም ቤተክርስቲያን ከየትኛውም ምዕራባውያን ሃገራት ካሉ ቤተዕምነቶች ጋር ግንኙነት እናዳይኖራት መንግስት በሰጣትም ስርአት እና ህግ እስከተዳደረች ደስረስ እንደሚቀጥሉ ነበር ይህንም ብዙ ፕሮቴስታንቶች ከስደት እንደ ተሻለ አማራጭ ያዩትም ነበር የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ግን ከቻይና ግዝት ውጪ የነበረችው ታይዋን ላይ መቀመጥን ምርጫቸው አድርገው መንግስት ያቀረበውን ሃሳብ ውድቅ አደረጉ። በዚህም ማኦ ዜዶንግ ስልጣን ላይ እስከነበሩበት እስከ 1976ዓ.ም ድረስ ማንኛውንም ሀይማኞታዊ እንቅስቃሴዎችን ከልክለዋል ፕሮቴስታንቶች የፈረሙት የመንግስት ሰነድም ረጅም ግዜ ለግልጋሎት ሳይበቃ ሃገረ መንግስቱ እስራትን እና በአማኞች ላይ እንግልትን ጀመረ በዚህም በቻይና ያሉ ቤተክርስቲያናት ሁሉ ተዘግተው፣ በድብቅ ወደ ሚደረጉ የቤት ለቤት ፕሮግራሞች ተለወጡ።

ከ1970ዎቹ ጀምሮ በቻይና መንግስት ለክርስቲያኖች መሰባሰብ የሚል የሚሰጥ ፈቃድ የለምና ብዙ ያልተመዘገቡና ፍቃድ አልባ

ቤተዕምነቶች ይገኛሉ። ያኔ የነበረው እንግልት እና እስራት ዛሩም በ21ኛው ክፍለ ዘመን ቀጥሏል በግዛቷ ስደት እና እስራት አይበዛባቸውም ተብለው በሚነገርላቸው Henan, Anhui and Zhejiang ከተሞች ቻይና ውስጥ ካሉ መቶ ሚሊዬን አማኞች በእነዚህ ግዛቶች ብዙ ቁጥር ያላቸው አማኞች ይኖራሉ። በዚህም በ2014 በተሰራ ጥናት ከ30 - 40 ሚሊዬን የሚሆኑ አማኞች በእነዚህ ከተሞች ይኖራሉ።

ከእንደዚህ አይነት ነባራዎ ሁኔታ፣ በአማኞች ላይ ከሚደርሰው እንግልት እና ስደት አኳያ የትም ያህል ፈቀቅ የማይል የሚመስለው የወንጌል ሩጫ ሌላ ተስፋን የሚያጭር መልካ በቻይና አለው። በብዙ የሚሲዮን ተቋማት የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በየቀኑ በቻይና በትንሹ 10,000 ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይጨመራሉ፣ ቤትለቤት ቤተክርስቲያኖች ውስጥ ያለው ስደትን ተቋቁሞ ወንጌልን የማድረስ ንቅናቄ በከፍተኛ ዉጥር እየጨመረ ነው ይህም ባቻ ሳይሆን የቻይና ቤተክርስቲያን በሚቀጥሉት አመታት ከ20,000 በላይ ሚሲዬናውያንን ወደ አለም ሁሉ ለመላክ "ባክ ቱ ጀሩሳሌም" የሚል እንቅስቃሴ መጀመራቸው ከበዛ ከመሰሰለው ጨለማ በላይ የሚፈነጥቅ ብርሃን ነው።

ይህን መሻት ለምድሪ ኢትዮጵያ እየተመኘው አማኞች ሁሉ በቻይና ላሉ ቅዱሳን ወንድም እና እህቶቻችን ጸሎታችንን እንድናበዛ እየተመኘው እዚሳ ጋር ላብቃ።

አማኑኤል ገዛኸኝ


የተዘጋ ቤተክርስቲያን


ለመንግስት የለውጥ ትምህርት የተላኩ አማኞች